# ፖርኖግራፊ

## ፖርኖግራፊ  ምንድን ነው?

መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ
@Biblicalmarriage
አዘጋጅ፡
+251910337074(አብርሃም ጥላሁን)

# ባርነት



መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ
@Biblicalmarriage
+251910337074(አብርሃም ጥላሁን)
አዘጋጆች፥

# ፖርኖግራፊ ምንድን ነው?

- ‘πορνογραφία’ (pornographia) ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን በጥንት

ጊዜ የቃሉ ትርጉም ስለ ሴተኛ አዳሪ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያትት ማናቸውም አይነት የስነ ፁህፍ ወይም የስነ ጥበብ ስራ ማለት ነው።

- በአሁኑ ዘመን ይህ ከጽሁፍ እና ስዕል ወደ ቪዲዮ ምስል ማደጉን እናያለን
- ማንኛውም የወሲብን ስሜት የሚቀሰቅሱ ወሲባዊ ታሪኮች፣ ፊልሞች፤ ፎቶግራፎች እንዲሁም የቃላት ልውውጥ

# ስለ ፖርኖግራፊ ጥናቶች ምን ይላሉ?

- ስለፖርኖግራፊ የተሰሩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ለፖርኖግራፊ ተጋላጭ የሚሆኑት ከ11 ዓመታቸው ጀምሮ ነው።
- በኢንተርኔት ውስጥ ከሚገኘው ወደ ግማሽ የሚሆነው መረጃ ፖርኖግራፊ ወይም ከፖርኖግራፊ ጋር ተያያዥ የሆነ መረጃ ነው።
- በየቀኑ ኢንተርኔት ከሚጠቀሙ ሰዎች መካከል 25% የሚሆኑት ፖርኖግራፊ የሚመለከቱ ናቸው።
- ከኢንተርኔት ላይ ከሚወርዱ ቪዲዮዎች መካከል 35% የሚሆነው ከፖርኖግራፊ ጋር የሚገናኙ ናቸው ።

# የቀጠለ....

- 34% የሚሆኑት የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ሳይፈልጉት በማስታወቂያዎች በራሳቸው ብቅ በሚሉ ሌሎች መረጃዎች ምክንያት ለፖርኖግራፊ ይጋለጣሉ።
- አለም ላይ ካሉ ድህረ ገጾች መካከል 12% የሚሆነው የፖርኖግራፊ ገጾች ነው።
- በአለማችን ላይ ከፍተኛ ገንዘብ ከሚያገኙ ሰዎች መካከል፣ በፖርኖግራፊ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ሰዎች ይገኙበታል።
- በሰሜን ኮሪያ በሐገሪቱ ውስጥ ፖርኖግራፊ ነክ የሆኑ ነገሮችን ማሰራጨትም ሆነ ማየት በሞት የሚያስቀጣ ነው።

# ሰዎች ለምን ፖርኖግራፊ ይመለከታሉ?

1. ደስታን ፍለጋ
2. ጭንቀት/ድብርት
3. ብቸኝነት
4. በጓደኛ ግፊት
5. ሱስ

- ሱስ ማለት ፈልገን የገባንበት ኋላ ግን እየጠላነውም ቢሆን የምናደርገው ነገር ነው።

መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ
@Biblicalmarriage
+251910337074(አብርሃም ጥላሁን)
አዘጋጆች፡

# የፖርኖግራፊ ሱሰኝነት ምልክቶች እና መዘዞቹ

1. ከፍተኛ ፍላጎት
2. ለማቆም አለመፈለግ / አለመቻል
3. በሌላ ነገር ደስታ አለማግኘት
4. ከተጽኖው ጋር መቀጠል
5. ሚስጥራዊነት
6. ኃላፊነትን አለመወጣት
7. የፀባይ መቀያየር

# የፖርኖግራፊ መዘዞች

- ከእግዚአብሔር ይለያል
- ድብርት/ጭንቀት
- አቅምን ይገለል
- ላልተፈለገ ተግባር ያጋልጣል
- የተሳሳተ አመለካከት
- ትዳርን ይበጠብጣል

መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ
@Biblicalmarriage
አዘጋጅ፡
+251910337074(አብርሃም ጥላሁን)

• **መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፖርኖግራፊ ምን ይላል?**

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ ብዙ የተፃፉ ክፍሎች ቢኖሩትም ስለፖርኖግራፊ ይህ ነው ተብሎ በግልፅ የተፃፈ ነገር አናገኝም። ሆኖም ግን ክርስትና በአካል ከሚደረጉ ሃጢያቶች ከመራቅ ባለፈ የአይምሮ ንፅህናን የመጠበቅ ጉዳይ እንደሆነ ያትትልናል። በዘፀአት 20 :17 ላይ “የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ” ሲል ሆነ፤ ክርስቶስ በማቴዎስ 5:27-29 “ሴትን በምኞት አይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል’’ ሲል፤ እንዲሁም በተለያዩ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የስጋ ምኞት ‘ነፍስንም የሚወጋ’ ኃጢያት (1ጴጥ 2:11) ተብሎ ሲጠቀስ እነዚህን ክፍሎች ከፖርኖግራፊ ጋር አያይዘን ልንግርባቸው እንችላለን። የስጋም ምኞት ኃጢያትን እንደምትወልድ፤ ኃጢያትም ሞትን እንደሚወልድ ይናገራል። (ያቆ 1:14-15) የፖርኖግራፊ ዋና ግብ የስጋን ምኞት መፍጠር ሲሆን ያም ሀጢያትን ይወልዳል፤ ኃጢያት ደግሞ ሞትን!

# ክርስቲያን እና ፖርኖግራፊ

• ማንኛውም ክርስቲያን እግዚአብሄር ኃጢያትን ጨምሮ ማናቸውንም ነገር ማሸነፍ እንደሚችል፤ ሁሉን ቻይ እንደሆነ እና ክርስቶስም ማናቸውንም ፈተና ልንቋቋም የምንችልበት ፀጋ እንደሰጠን ቢያምንም በፖርኖግራፊ ሱስ እየታገለ ያለ ክርስቲያን ግን ይህን እውነት መጠራጠር ይጀምራል። ከብዙ ፀሎት፣ ለእግዚአብሔር እና ለራስ ከሚደረግ ከብዙ ቃል መኃላ፤ ጥረት እና ትግል በኋላ ራሱን በሱስ ውስጥ መልሶ ወድቆ ሊያገኘው ይችላል። በእርግጥ እግዚአብሔር አለ! በእርግጥ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው! ሆኖም ግን እኛ እንደምንፈልገው ነፃ መውጣት በአንዴ ላይሆን ይችላል። በዚህ ሱስም ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖችም ከዚህ አንፃር በቤተ ክርስትያን ካለው መገፋት እና ኃፍረት የተነሳ መፍትሄን ከመፈለግ ያፈገፍጋሉ። ይህም ግለሰብ በቤተክርስትያን አገልግሎት ወይም መሪነት ቦታ ካለ ነገሮችን የበለጠ የተወሳሰቡ ይሆናሉ። ሰው ችግሩን አምኖ የሚመጣው ይምጣ ብሎ እርዳታን መፈለግ ግን በሱሱ ዘልቆ ከሚመጣው ጉዳት አይብስም። በኋላ እግዚአብሄር ፍርድ ፊት ከመቅረብ ዛሬ ላይ በሰው ፍርድ ውስጥ ማለፉ የተሻለ ነው።

# ከፖርኖግራፊ ሱስ መውጫ መንገዶች

1. እግዚአብሔር እንደሚወዳችሁ አውቃችሁ ንሰሐ ግቡ
2. አምናችሁ ጸልዩ
3. ሀሳብን በሀሳብ ተዋጉ
4. ለምን እንደምታዩ እወቁ
5. ቀስቃሽ ነገሮችን ለዩ
6. ታገሉ
7. ስሜቶቻችሁን ተቆጣጣሩ
8. ብቸኝነትን አስወግዱ
9. ተስፋ አትቁረጡ
10. ግልጽ ሁኑ

- * Covenant Eyes እና X3 Watch፣ ማንኛውንም ፖርኖግራፊ ነክ ምስሎች ወይንም ፅሁፎችን ብሎክ በማድረግ፣ ከዚህ ሱስ
- እንድንወጣ የሚረዱን፣ ለሞባይልና ለኮምፒውተር የተዘጋጁ የሶፍትዌር ፕሮግራሞች ናቸው።

- በፖርኖግራፊና ግለ ወሲብ/Masturbation/ ሱስ ተይዛችሁ የምትጨነቁ ወገኖቻችን በማንኛውም ጊዜ ልንረዳችሁ ዝግጁ ነን። በ+251910337074 ወይም +251912443544 ላይ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ድረስ ይደውሉልን። ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆኑ በቫይበር፣በቴሌግራም፣ በኢሞና፣ በዋትስአፕ ሊያገኙን ይችላሉ።

# ምንጭ

- Ermias Kiros, Daily Injera



# STOP PORNOGRAPHY